# PENSER C’EST   SAVOIR DIRE NON !!

# *ማሰብ ማለት በደልን እንቢ ማለት ማወቅ ነው !!*

*አሥራደው (ከፈረንሳይ)*




*ማስታወሻ :*

*ሃሳባቸውን በየጊዜው ለሚያካፍሉኝ ወንድሞቼና እህቶቼ በሙሉ ምስጋናዬን እያቀረብኩ አንድ ወንድሜ « አቶ መለስ ዜናዊን አንተ ለማለት እንኳን የሚቀፍ ፍጡር ሆኖ ሳለ፤ ለምን አንቱ እያልክ ትጽፋለህ » ? ብሎ ለጠየቀኝ ጥያቄ ጥቂት ለማለት እወዳለሁ ::*

*አቶ መለስ ዜናዊና መሰሎቻቸውን ከተጠናወታቸው የጥላቻ፤ የዘረኝነት፤ የስድብ፤ የዋልጌነት፤ የአንባ ገነንነት፤ የነጭ አምላኩነት፤ የዲፕሎማሲ መሃይምነት፤ በጥቅሉ የስነምባር ድህነት ለማላቀቅ፤ አማራጩ ኢትዮጵያዊ ጨዋነትና ክብር እንዲማሩ ለማድረግ፤ እንደነሱ በመቅለል ሳይሆን፤ ከነሱ የምንለይበትን ኢትዮጵያዊ ጨዋነትና ሰው አክባሪ ስነ ምግባሮችን እንዲማሩ እድሉን ለመስጠት እንጂ፤ የአቶ መለስ ዜናዊ ሰብዕና ለአንቱታ እንደማይበቃ ከሚረዱት ሰዎች አንዱ ነኝ ::*

*ሌላው ኢትዮጵያን የሚያህል ታሪካዊና ትልቅ አገር በሕዝብ ፍላጎት ሳይሆን በአጋጣሚ የሚመሩ በመሆናቸው ለሳቸው ሳይሆን ለአገሬ ለኢትዮጵያ ክብር ስል ነው ::*

*አገሬ፤ ሰንደቅ ዓላማዬ፤ ቋንቋዬ፤ ባሕሌ፤ ሃይማኖቴ፤ የአስተዳደግ ስነስርዓራቴ እንዲሁም የዕውቀት ደረጃዬ፤ ለማንኛውም ሰው ክብር ሰጥቼ ክብርን እንድቀበል ያስገድዱኛል :: እንግዲህ ወንድሜ የተረዳኸኝ ስለሚመስለኝ በዚሁ ላብቃ፤ ለአስተያየትህ ከልብ አመሰግናለሁ::*

## መግቢያ ፡

ሰው ያልሆነ ሰው የሰው ጥላ፤ ሌሎች ያሉትንና የሠሩትን ከመድገም በቀር የራሱ የሆነ ይህ ነው የሚለው ፈጠራ የሌለው፤ እሱነቱን ሳይሆን ሌላው ያለውን ሆኖ፤ የሱን እሱነት ውጠ በሌላው እስትንፋስ ሲያቃትት፤ የራሱ ነብስ የሲቃ ጩኸት ስትጮህ ጩኸቷን ሳለመስማት ጭንቅልቅቱን በሸንፍላው ውስጥ ቀብሮ እያንኳረፈ፤ እሱነቱን በራሱ የዓይነ ሕሊና መስታወት መመልከት ተስኖት እየተደናበረ፤ የዘመነኞችን የጥጋብ ግሳት እያሸተተ አረፋ በመድፈቅ፤ በጣዕረ ሞት ገላው ላይ የሕግ ጥብቆ አጥልቆ፤ የዘመነኞች ወዘና ሲንጠፈጠፍ የሱን አመዳምነት ያወዛ ይመስል፤ የሕግ ተገዢ ነኝ ይላል የደከመ አጥሙን በሞት አፋፍ ላይ በሸንበቆ ከዘራ ደግፎ ።

አንደበቱ በግፍ ማነቆ ታንቃ ህቅ ስትል ብሶቱን ውጠ በሌሎች ቋንቋ ሲያንቧርቅ፤ ልቡ የመጨረሻዋን የደም ጠብታ ስታለቅስ ሳለመስማት ጆሮውን ደፍኖ፤ የጋሪ ፈረስ ሆኖ፤ ሲስቡት ተስቦ፤ ሲገርፉት ተገርፎ፤ ሲነጥቁት ተነጥቆ፤ ሲያስሩት ታስሮ፤ ሲገሉት ተገሎ ይኖራል፤ **እንቢ !!** ማለትን ፈርቶ፡፡ ይህ ልበ ሙት ነሆለል መብቱን ተገፎ ምልምል ገላውን ራቁቱን ቆሞ ።

እናም ተረዳ፤

**ማሰብ ማለት በደልን በዝምታ አልቀበልም  እንቢ ማለትን ማወቅ ነው !!**

ወያኔዎች ለዘረፋ እንጂ አገር ለማስተዳደር አልመጡም፤ ያውም ከተራበ ወገናቸው ነጥቀው የሚበሉ፤ በውስጣቸው ርህራሄ ያልተጠፈጠረ የገዛ ወገኖቻቸውን ለስልጣን ሲሉ በረሃብ የፈጁ፤ በነፃ አገር እየኖሩ ዛሪም ከሃያ ዓመት በኋላ እንኳን የአንድ ክፍለ ሃገር የትግራይ (ህወሃት) ነፃ አውጪ ድርጅት ነን የሚሉ ናቸው ። ታዲያ በኢትዮጵያ ስም የልመና አቁማዳ ይዞ ልመና እየተቀፈፈ፤ ከኛ አልፎ የልጅ ልጆቻችን ሊከፍሉት የማችሉት ብድር በኢትዮጵያ ሕዝብ ስም እየተነከሩ፤ (በወርቁ ዘር ! እንደሳቸው አባባል) በትግራይ ስም የሚበላው እስከመቼ ነው ?!

በ21ኛው ክፍለ ዘመን መባቻ፤ በጀርመን የዘር ግንብ በሕዝብ ፍቅር ሲናድ፤ ወያኔዎች በትግራይ ሕዝብና፤ በቀሪው ኢትዮጵያዊ ወገኖቹ መሃል አሳፋሪ የዘር ግንብ ለመገንባት ደፋ ቀና ይላሉ፤ የትግራይ ወንድሞቻችንና እህቶቻችንን እኛ ቀሪው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዛሬ የምንጠይቃቸው ከራስ አልፎ ለልጅ ልጅ የሚተርፍ ቂምና ጥፋት ከመድረሱ በፊት አሰበው፤ አብረውን እንዲነሱ ነው ።

**ማሰብ ማለት አሳፋሪ የዘረኝነት ግንብ በመሃላችን ሲገነባ እንቢ ማለትን ማወቅ ነው !!**

አበው « ዝቅዝቅ የዶሮ ሽክም !! » እንዲሉ ፤ ትናንት የቅኝ ተገዢ የነበሩ እንደ ሕንድ፤ የአረብ አገሮችና ቻይና ጭምር በነፃነቷ ከራሷ አልፋ ለቀሪው ዓለም በምሳሌነት የምትጠቀሰው የኢትዮጵያ፤ ልጆች « መሬት ላራሹ !! » በሚል መፈክር በደማቸው የዋጁትን መሬት ከድሃ ገበሬው እየነጠቀ በዶላር ቸብችቦ አገራችንን የነዚህ ዝርክርክ አገሮች የቆሻሻ መጠራቀሚያ ከማድረጉ በፊት በአንድነት ለራሳችን፤ ለልጆቻችን፤ ለአገራችን ክብር ሰንል በጋራ እጅ ለእጅ በመያያዝ፤ እንቢ ማለት አለብን ::

ማሰብ ማለት አገር ሲሸጥ እንቢ ማለትን ማወቅ ነውና !!

ወያኔ የራሱን ዘረኝነት ወርቅ ቀብቶ፤ በመጀመሪያ አማርኛ ተናጋሪውን ትምክተኛ፤ ቀጥሎ ኦሮምኛ ተናጋሪውን ሽብርተኛ፤ አስከትሎም ጉራጊኛ ተናጋሪውን አሻጥረኛ፤ በማለት ስልጣኑን፤ መሬቱን፤ የአገሪቱን ሃብት፤ ኢኮኖሚውን በአንድ ዘር እልፍም ብሎ በአንድ የማፍያ አጋሚዶ ቡድን ጠቅልሎ በመያዝ ሕዝቡንና አገሪቱን አራቁቶና አደህይቶ ብሎም ለባዕድ ሽጦ አገር አልባ እርጎ ሳያስቀረን፤ አንዱን ነጥሎ ሲመታ፤ ሌላው ነግ በኔ በማለት በአንድላይ ለአገራችን፤ ለመብታችንና ለሰብዕናችን በጋራ ዘብ መቆም አለብን ::

ማሰብ ማለት ግፍ በወገኖቻችን ላይ ሲሠራ እንቢ ማለትን ማወቅ ነው !!

የአንድ አገር ትልቁ ሃብቷና የመኖሯ ህልውና ሕፃናትና ወጣቱ ትውልድ መሆኑን ባለመዘንጋት ወያኔ በዶላር የሚቸበችባቸውን ኢትዮጵያዊ ሕፃናትን መታደግ፤ ወጣቱን ትውልድ : ለአገሩና ለወገኑ ብሎም ለራሱ ህልውና ሲል : የወያኔን ጭቆና እንዳለፉት ወጣቶች በጋራ በመታገል : ለድል እንዲበቃ መርዳት እንጂ: አገር ጥሎ እንዲሰደድ ማድረግ : ወያኔ « ሂድ አትበለው ግን እንዲሄድ አድርገው » ብሎ ያወጣውን የዘረኝነት መፈክሩን መካፈል ስለሚሆን : ወጣቱ አገሩን ጥሎ እንዳይሰደድ: እኛም ሁኔታዎችን በማመቻቸት አብረናቸው ለአገራችንና ለሕዝባችን ለመዋደቅ መዘጋጀት አለብን ::

ማሰብ ማለት ሕፃናት አይሸጡም ወጣቱ አይሰደድም እንቢ ማለትን ማወቅ ነው !!

ወያኔ ብዕርን እንደጦር ይፈራል፤ ብዕር በሕዝብ ላይ እስትንፋስን እፍ በማለት : ሕይወት እንደሚዘራና ለመብቱ እንዲቆም ስለሚያደርግ፤ ወያኔ ደግሞ : ሕዝብን በዝምታ ባሕር ውስጥ ዘፍቆ : በፍራቻ አፍኖ መግዛት የዘውትር ህልሙ በመሆኑ : ብዕርን ይፈራል ይረግማልም :: ብዕር ላነሱ በብዕር መመለስ ስለማይሆንላቸው በብዕር ለተጻፈ መልሳቸው የጠመንጃና የታንክ ጥይት ነው : አስተሳሰባቸው በዘረኝነት የታጠረ ነውና ::
ሆዳም ምሑር ተብዬዎችን : በዶለዶመ ብዕር የታሪክ ዲሪቶ እንዲደርቱላቸው : ከሕዝብ ከዘረፉት ሃብት ፍርፋሪ : እየወረወሩላቸው ሲደነቁሉ ቢውሉም፤ የኢትዮጵያ ታሪክ : በብርቅዬ ልጆቿ ደም የተጻፈ በመሆኑ መደለዙ ቸግሯቸዋል ::
« አክሱም ለናንተ ምናችሁ ነው ? » እንዳላሉን አስመሳዩ መሪ : ሰሞኑን በዓባይ ስም ሲምሉ ሰንሰማ : የማሰብ ችሎታቸው ከቁመታቸው ዘልግ እንደማይል መገንዘብ ችለናል: :

*ዓባይን ለኛ፤ ዓባይን ለሕዝባችን ይተውልን: እኛና ዓባይ አንድ ቋንቋ ስለምንነጋገር እንግባባለን: ቋንቋችንም አንዲት ኢትዮጵያ ብቻ ናት ::*

*የምንጽፈው እንቶኔ ፍቃድ ስለሰጠን ሳይሆን፤ መጻፍ የማሰብ ነፃነታችን ፍሬ በመሆኑ ሳይማር ያስተማረን ሕዝባችን ከግፍ አገዛዝ ነፃ እስከሚወጣ ሳናሰልስ እንጽፋለ ! ጻፉ ! ብዕራችን እንደ በላይ ዘለቀ፤ አሉላ አባ ነጋ፤ ዘርአይ ደረስ፤ አብዲሳ አጋ፤ ኃይለማርያም ማሞ፤ ገረሱ ዱኪ፤ ኡመር ሰመተር፤ ሙሉጌታ ቡሊ፤....ወዘተ የመሳሰሉ ለአገራቸውና ለሰንደቅ አላማቸው የወደቁ ጀግኖችን በመዘከር የነሱን ፈለግ የሚከተሉ ሺህ ወጣቶችን አገራችን ታፈራለች: ከዚያም በወያኔ የተረገጠው ሰንደቅ ዓላማዋን በተራሮቿ ላይ ከፍ አድርገው በኩራት ያውለበልቡታል::*

*እናም፤ ማሰብ ማለት አልታፈንም እንቢ እጽፋለሁ ማለትን ማወቅ ነው !!*

*ማሰብ ማለት አልታሰርም እንቢ ማለትን ማወቅ ነው !!*

*ማሰብ ማለት በግፍ አልገደልም አልሞትም እንቢ ማለትን ማወቅ ነው !!*

*ማሰብ ማለት ግብር ለመክፈል እንደ ወንጀለኛ የጣት አሻራ አልሰጥም እንቢ ማለትን ማወቅ ነው !!*

*ማሰብ ማለት የአገር ሃብት አላዘርፍም እንቢ ማለትን ማወቅ ነው !!*

*ማሰብ ማለት በብድር አንዘፈቅም እንቢ ማለትን ማወቅ ነው !!*

*ማሰብ ማለት በልመና አንኖርም እንቢ ማለትን ማወቅ ነው !!*

*ማሰብ ማለት « መከልከል ክልክል » ነው ማለትን ማወቅ ነው !!*

*ማሰብ ማለት በደልን በቃኝ እንቢ ማለትን ማወቅ ነው !!*

*በመጨረሻ ማሰብ ማለት የማሰብ ነፃነቴን አላስነጥቅም እንቢ ማለትን ማወቅ ነው*

*ጎበዝ ! እስቲ ስንቶቻችን ማሰብ አንችላለን ??!!*

*ማሰብ ከቻልን ወያኔን ማስወገድ አያቅተንም !!*

*እናስብ ! እንተባበር ! በአንድላይ እንነሳ !*

*ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !!*

*እግዚአብሔር ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ይባርክ !!*

*ታኅሣሥ 24 ቀን 2003 ዓ.ም. (Janwary 2/ 2011)*